# ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች የወጣውን መመሪያ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

# ቁጥር 88/2006

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ጥቅምት 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች የወጣውን ደንብ ለማስፈጸም የወጣውን መመሪያ ቁጥር 66/2004 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 88/2006**

ያለውጭ ምንዛሪ ለቤተሰብ፣ለዘመድና ለጓደኛ ከውጭ አገር የሚላኩ በስጦታና በልገሳ የሚገቡ ያገለገሉ አልባሳት በጤና እና በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪው ላይ የፈጠሩትን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ፣

በስጦታና በልገሳ የሚላኩ ዕቃዎች መጠን ያለመወሰኑ በሕጋዊ ነጋዴ ተፎካካሪነት ላይ የፈጠረውን አሉታዊ ተፅዕኖ መቀነስ በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በደንብ ቁጥር 88/1995 አንቀጽ 3(1) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይኸን የተሻሻለ መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ “ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች የወጣውን መመሪያ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 88/2006” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡
2. **ማሻሻያ**
   1. የመመሪያው አንቀጽ 5 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ተተክቷል፡፡

      5. **ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ የሚገቡ ዕዎቃች**

      1/ ያለውጭ ምንዛሪ የሚገቡ ዕቃዎች ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ ባለው ሠንጠረዥ በተገለፀው ሁኔታ ዓይነትና መጠን ወደ ሀገር ይገባሉ፡፡

      2/ በተያያዘው ሠንጠረዥ ተራ ቁጥር 10 የተገለፁት ዕቃዎች ፡-

      ሀ. ጠቅላላ የ”FOB” ዋጋቸው ከ1000 /አንድ ሺህ/ USD የማይበልጡ ሆነው ያገለገሉ አልባሳትን እና ጫማዎችን ማስገባት አይፈቀድም፡፡

      ለ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) በተገለፀው መጠን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከ2 (ሁለት) ጊዜ በላይ በስጦታ ወይም በልገሳ የተላከ ዕቃ ወደ አገር ማስገባት አይቻልም፡፡

      ሐ. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለመመሪያው አፈጻጸም ተገቢውን መረጃ የመያዝና በዚሁ መሰረት የመፈጸም ሃላፊነት አለባቸው፡፡

3. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣ ከ10 ቀናት በኂላ በተጫኑ ዕቃዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

በከር ሻሌ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር